# Initial Diagnostic, Corrective Measures & Engagement

**የፍተሻ መነሻ ፣ የማስተካከያ ሥራዎች እና ተሳትፎ**

## 1. አጠቃላይ

ይህ ሰነድ የጥገና አጀማመርን፣እያንዳንዱን የአተገባበር ሂደትን፣ለጥገናው ኃለፊነት የሚወስደውን አካል፣ለጥገናው መሟለት ያለበትን ሰነድ እና የማላመድ ዘዴው እንዴት መተግበር እንዳለበት ያስቀምጣል።

**ቁልፍ ትርጉም**

### 1.1 ፍተሻ

የፍተሻ ቼክሊስቱን በመጠቀም ተቋሙን በመገምገምና መረጃ በማደራጀት የኔትወርኩን ችግሮች መለየት ያስፈልጋል። የሁሉም ቦኖ ፍተሻ የሚጠናቀቀው ጥቅምት ወር ሲሆን ይህም የማስተካከያ ሥራውን ለመለየት ይጠቅማል፥

### 1.2 የማስተካከያ ሥራዎች

በፍተሻው ደረጃ ላይ የተገለጹትን ችግሮች ለመፍታት መከናወን ያለባቸው ሥራዎች ናቸው።

የማስተካከያ ሥራዎች የሚከተሉትን ሊሆኑ ይችላሉ፡-

- ቴክኒካል ይዘት ያለው ድርጊት ሊሆን ይችላል

*ለምሳሌ :- ያልተቀበረ እና የተጋለጠ ቧንቧ መስመር ማስተካከያ ሥራ = ቧንቧ የተጋለጠበት ቦታ ላይ ካብ መገንባት እና አፈር ማልበስ*

- ወይም መደበኛ/ተደጋጋሚ እንክብካቤ መልሶ ማደራጀት ያስፈልግ ይሆናል፣

*ለምሳሌ፡- የውሃ ቦኖውና አካባቢው በጣም ቆሸሾ መገኘት። ማስተካከያ ሥራ = የቦኖ ዕለታዊ ጽዳት ሥራ ማደራጀት*

### 1.3 የደረጃ አሰጣጥ

የደረጃ አሰጠጥ አጠቃላይ የፍተሻ ውጤት ማሳያ ሆኖ በቀላሉ በደሽቦርድ የሚገለጽ እና ለወ/ው/ጽ/ቤት በሪፖርት የሚገለጽ ነው።

የደረጃ አሰጣጡ ሥርዓት ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል።

### 1.4 ሥልጠና

የሥልጠናው ሥርዓት ለአጠቃላይ ጥገናው ሂደት እና አስተሳሰብ ለውጥ አስፈላጊ ክፍል ነው።

### 1.5 የማስተካከያ ሥራው ተሳትፎ

በወ/ው/ጽ/ቤት እና በፌዴሬሽን ተሳትፎ የተዘረዘሩ የማስተካከያ ሥራዎች በጥገና ዘመቻ ወቅት የሚፈቱ ይሆናሉ።

### 1.6 የጊዜ ሠሌዳ/ካላንደር

ይህ ዘዴ በጥቅምት እና ኅዳር የሚከናወኑትን ከጥገና ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ያብራራል፡-

| ወር | ተግባራት | ፈጻሚ | ዘዴ |
|---|---|---|---|
| ጥቅምት | የፍተሻ ቼክሊስት፣ የማስተካከያ ሥራ ማብራሪያ እና የቦኖ ደረጃ አሰጣጥ | የውሃ ተጠሪ እና ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | WS3-M11 |
| ኅዳር | ለውማሬ እና ለውማ ተወካች የማስተካከያ ሥራውን ማሳወቅ<br>የተለየውን የማስተካከያ ሥራው ላይ ተሳትፎ ቃል ኪዳን የሚገቡበት የፍርማ ሥነሥርዓት | ውማሬ እና ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | |
| ታኅሳስ | ፍተሻውንና የተለየውን የማስተካከያ ሥራ ትክክለኛነት በናሙና ደረጃ ማረጋገጥ | ዞን እና አርአያ | WS3-M17 |
| ጥር | የጥገና እቅድ<br>የመደበኛ ጥገናውን ሥራ ማደራጀት እና ፈር ማስያዝ | የውሃ ተጠሪ እና ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | WS3-M14<br>WS3-M13 |
| ከጥር እስከ መጋቢት | ጥብቅ በሆነ የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ክትትል ጥገናውን ማካሄድ(የመጨረሻ የጊዜ ገደብ መጋቢት 30) | የውሃ ተጠሪ እና ውማ (በወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ቴክኒካል ድጋፍ) | WS3-M16 |
| ሚያዚያ | በወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ የተረጋገጠው የማስተካከያ ሥራ ሪፖርት እስከ ሚያዚያ መጨረሻ ድረስ እና 100% ከተጠናቀቀው የ"B" ጥገና ሪፖርት ጋር ይላካል | ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | |
| ግንቦት | መደበኛ እንክብካቤ እና የማስተካከያ ሥራው በትክክል መከናወኑን በናሙና ማረጋገጥ(ምንጭ እና ቦኖ) | ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | WS3-M18 |
| ሰኔ | ማስተካከያ ሥራው መሰራቱን በናሙና ማረጋገጥ | ዞን እና አርአያ | |

*በዚህ ቀለም የተጠቀሱት፣ የትግበራ ቅደም ተከተል ናቸው : መንግስትና አርአያ የመስክ ሰራተኞችን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል*

*በዚህ ቀለም የተወከሉት፣ ሥራዎች መፈጸማቸውን የማረጋገጥ ቅደም ተከተል የሚያሳዩ ሲሆኑ የሚከናወኑትም በመንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እና አርአያ ጥምረት ነው*

## 2.ፍተሻ እና የማስተካከያ ሥራ ልየታ

### 2.1 የፍተሻ ዓይነቶች

ፍተሻ እና የማስተካከያ ሥራ ለሁሉም የሚሠራ ቦኖ ለእያንዳንዱ ፌዴሬሽን መሠራት ይኖርበታል።

የፍተሻ ሥራውም መከናወን ያለበት ከምንጭ እስከ ቦኖ ድረስ፣ የቧንቧ መስመር ተከትሎ ሁሉንም የተቋሙን ክፍሎች ቅኝት በማድረግ መሆን ይኖርበታል።

የተቋሙን መዋቅር ብቻ ፍተሻ አድርጎ በኔትዎርኩ ላይ ከፍተኛ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ለምሳሌ ያልተቀበረ ቧንቧ፣ የወንዝና መንገድ መሻገሪያዎችን ቸል ማለት ፍተሻውን ሙሉ አያደርገውም።

### 2.2 ኃላፊነት

የኔትዎርክ ፍተሻ መደረግ ያለበት የቧንቧ መስመሩን ተከትሎ እስከ ቦኖ ድረስ ሲሆን ሁሉንም የተቋሙን ክፍሎች ቅኝት በማድረግ የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ከውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ጋር በጋራ በመሆን ይኖርበታል።

ይህንን ተግባር በዋናነት ማከናወን ያለበት የውሃ ተጠሪ ነው።

የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ሥልጠና/ድጋፍ የመስጠት (የቴክኒክ እና የአስተሳሰብ ለውጥ የማምጣት ክህሎት የማስተላለፍ) እና ውሃ ተጠሪውን የመቃኘት/የመቆጣጠር ኃላፊነቱን ይወስዳል።

የውማ ፍተሻ በሚደረግበት ወቅት በጋራ ይከታተላሉ።

### 2.3 መረጃ ማደራጀት

የውሃ ተጠሪው **“የፍተሻ ቼክሊስቱን n°WS3-F11-V1.0** ይሞላል። (የፍተሻ መዝገቡ መኖሩን እና መደራጀቱን እንዲሁም ለአንድ ተቋም አንድ ገጽ መኖሩን አረጋግጥ)።

የውሃ ተጠሪው የቼክ-ሊስቱን እያንዳንዱን መስመር ድምጹን ከፍ አድርጎ በሚያነብበት ወቅት የውሜ አባላት በመስማት ችግሩን በአካል ይመለከታሉ።

ለምሳሌ፡-

**የተፋሰስ *ሥራ*፡-** ማስፈለግ አለማስፈለጉን መለየት የሚችሉት ከሚንጩ በላይ በኩል ሄደው በመመልከት ይሆናል፡፤

**በምንጭ ሳጥን ውስተጥ ደለል እና *ሥራሥር*፡-** መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ የሚቻለው የምንጩን ሳጥን ከፍቶ በማየት ይሆናል

**የትርፍ ውሃ ማስወገጃ፡-** መደፍን አለመደፈኑን ማረጋገጥ የሚቻለው ወደ ትርፍ ውሃ መውጫ ጫፉ ጋር በመሄድ ይሆናል

ውሃ ተጠሪው ቲክ √ ከማድረጉ በፊት ቡድኑ ስለሚፈተሸው ክፍል በሙሉ መስማማት ይጠበቅባቸዋል። ትንሽ ችግር ከተገኘበት X ይደረጋል።

ፍተሻው ሲደረግ ካልተስማሙ ወይም ችግር ካለበት (X)፣

- ለምን ይህ ችግር ሊፈጠር ቻለ?
- ይህንን ችግር ለዘለቄታው ለማስወገድ እንዴት አደራጅተን እንምራው? = መደበኛ የማስተካከያ እንክብካቤ

እንዴት ችግሩን እንቅረፍ/እንጠግን?= ቴክኒካል የማስተካከያ *ሥራ*

ምሳሌ፡-

ችግሩን ለመቅረፍ አንድ ብቻኛ የማተካከያ *ሥራ* ልንተገብር ይገባናል።

- የቦኖው ወለል ጭቃማ ቢሆን = ዕለታዊ የጽዳት *ሥራ* ማደራጀት(መደበኛ እንክብካቤ) ያስፈልጋል።
- ወንዝ/ሸጥ ሲሻገር ያልተሸፈነ ቧንቧ ካለ = ቧንቧ የተጋለጠበት ቦታ ላይ ካብ መገንባት እና አፈር ማልበስ(ቴክኒካል *ሥራ*)

ወይም ሁለቱንም ቴክኒካል የማስተካከያ *ሥራ* እና መደበኛ እንክብካቤ ማሻሻያ *ሥራ* በጥምረት ልያስፈልግ ይችላል።

- የቦኖው ዙሪያ በከብቶች እንቅስቃሴ ምክንያት ተሸርሽሮ እንደሆን የተሸረሸረውን ቦታ ላይ ካብ ለመገንባት እና አፈር ለማልበስ የ*ሥራ* ዘመቻ ቀን ማመቻቸት(ቴክኒካል *ሥራ*) እንዲሁም
- ለቦኖ ኮሚቴዎች ወርሃዊ የካብ እና አፈር የማልበስ ክትትል *ሥራ* ማመቻቸት (መደበኛ እንክብካቤ)



**3.** የማስተካከያ *ሥራ*ዎችን መደበኛ ማድረግ

### 3.1 ኃላፊነት

በፍተሻ ወቅት አንዴ የማስተካከያ ሥራው ከተለየ በኋላ የውሃ ተጠሪው በአግባቡ መዝግቦ ሊይዛቸው ይገባል።

ይህም መከናወን ያለበት፣ የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ባለበት በመስክ ወይም እሱ በሌለበት ከሆነ በፌዴሬሽን ቢሮ ሊሆን ይገባል።

### 3.2 መረጃ አያያዝ

<u>**Format n° WS3-F12 ማስተካከያ ሥራ መከታተያ**</u> ፎርማትን የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያው መሙላት ይኖርበታል

| PROCEED Doc n"Ws3-F12 Rev 1 የማስተካከያ ሥራ መከታተያ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀበሌ________ የውማ ስም________ | | | **የጥቅምት ወር ፍተሻ** | | |
| **የፍተሻ ችግር** | **መደበኛ እንክብካቤ ለውጥ** | **የማስተካከያ ሥራ ይፈልጋል** | **የ"B" ችግር** | | **የ"C" ችግር** |
| | | | **ውማ** | **ውማ/ውማፌ** | **ግንበኛ** |
| **የተቋም ዓይነት እና ስም (ከላይኛው ቧንቧ ጋር):** ________ 1 | | | | | |
| 2 | 3 ☐ | 4 | ☐ | 5 ☐ | ☐ |
| ለምንጭ እና ቦኖ | መደበኛ እንክብካቤ ሕጋዊ ማድረግ(አዎ/አይ) | | 6 | | |
| | መደበና እንክብካቤ ውጤታማነት(አዎ/አይ) | | | | |

❶ የተቋም ዓይነት( ለምሳሌ፡ ማጠራቀሚያ) እና ተቋሙ በአከባቢው የሚጠራበትን ስም ጻፍ

❷ በቼክ-ሊስቱ ላይ የተለዩ ችግሮችን ጻፍ( እያንዳንዱን ቼክሊስት *በ* **X** የሆኑትን በሙሉ ጻፍ )

❸ ከመደበኛ እንክብካቤ ጋር የተያያዘውን ችግር እና የመደበኛ እንክብካቤ ለውጥ የሚፈልገውን ቲክ አድርግ (ከታች ያለውን የመደበኛ እንክብካቤ ክፍል ተመልከት)

❹ የማስተካከያ ሥራ የሚያስፈልገውን ዘርዝር። የቴክኒክ እነ መደበኛ እንክብካቤ ሥራ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ሁለት መስመሮችን ተጠቀም፤ አንዱን መስመር ለአንዱ ማስተካከያ ሥራ

❺ የትኛው ሥራ በማን ይመራል የሚለውን ተገቢውን ሳጥን ለተገቢው ሰው ቲክ አድርግ

❻ በፍተሻ ቼክሊስቱ ላይ በግልጽ እንደተብራራው መደበኛ እንክብካቤ የጊዜ ሠሌዳ ያለ እንደሆን አዎን ብለህ ጻፍ

መሬት ላይ ከተተገበረ(አዎን)

ለምሳሌ፡-

- ረጃጅም ሥሮች በምንጩ ሳጥን ውስጥ ካለ እና መደበኛ እንክብካቤ ለማድረግ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ከሆነ፣ የውማ በዚሁ ፕሮግራም መሠረት በየወሩ የምንጩን ሳጥን ማጽዳት ይኖርባቸዋል።
- በቦኖ ወለል ላይ በርካታ ጭቃ ካለ እና መደበኛ እንክብካቤ ለማድረግ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ከሆነ፣ የውማ በዚሁ ፕሮግራም መሠረት በየቀኑ የቦኖውን ወለል ማጽዳት ይኖርባቸዋል።

በዚህ መሰረት መደበኛ እንክብካቤ የተደራጀ ነው ነገር ግን ውጤታማ አይደለም

- ተደራጅቷል በሚለው ላይ "አዎን" ብሎ መጻፍ

- የመደበኛ እንክብካቤው ውጤታማ ነው የሚለው ላይ "አይ" ብሎ መጻፍ

**ጥንቃቄ፡** በዚህ ደረጃ የውሃ ተጠሪው በኋላ ላይ ሊቀረፋ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ የማስተካከያ ሥራዎችን መንደፍ ይኖርበታል።

ለመደበኛ እንክብካቤም ተመሳሳይ ሎጂክ ልንከተል ይገባል። ሥራውን የማደራጀትና ተግባራዊ የማድረጉ ጉዳይ ምንም እንኳን ከኋላ ቢሆንም የውሃ ተጠሪው ወዲያውኑ በችኮላ ለመሥራት መነሳት የለበትም።

## 4. የደረጃ አሰጣጥ

የደረጃ አሰጣጥ አጠቃላይ የፍተሻ ውጤት ማሳያ ሆኖ በቀላሉ በደሽቦርድ የሚገለጽ እና ለወ/ው/ጽ/ቤት በሪፖርት የሚገለጽ ነው።

| ደረጃ | ተቋሙ ምን ይመስላል | ምን መሠራት አለበት | ይህን ማን ሊጠግን ይችከላል |
|---|---|---|---|
| A/U | ቦኖ እና ጠቅላላ ኔትዎርኩ **እንከን አልባ ሲሆን** | መደበኛ እንክብካቤ እና ፍተሻ | የቦኖ ኮሚቴ፣ ውማ እና ውተ |
| B/ለ | ቦኖ እና ኔትዎርኩ የሚሠራ ሆኖ ቀለል ያለ ጥገና የሚፈልግ<br>ከባድ ችግር ያልሆነ እና በቀበሌ ደረጃ ሊፈታ የሚችል(በማህበራት፣በፌዴሬሽን፣ቁል | የመከላከል ወይም የማስተካከያ ጥገና=መልሶ ግንባታ፣መደበኛ እንክብካቤ ማደራጀት | በወ/ው/ጽ/ቤት ድጋፍ በውተ እና ፌዴሬሽን የሚሠራ |
| C/ሐ | ቦኖ እና ኔትዎርኩ የሚሠራ ሆኖ ከባድ ጥገና የሚፈልግ<br>ይህንን ከባድ ጥገና ለማከናወን የሠለጠኑ | ጠቅላላ ሥርዓቱ ከባድ መልሶ ግንባታ ይፈልጋል | ፌዴሬሽን በወ/ው/ጽ/ቤት እና በኮንተራክተሮች ይደገፋሉ |
| D/መ | ቦኖ እና ኔትዎርኩ የማይሠራ ሆኖ ከባድ ጥገና ይፈልጋል። ጥገናው በአካቢ ሞያተኞች የማይሠራ ነው።(ነገር ግን ውሃ በምንጩ ይገኛል) | ሙሉ በሙሉ እንደገና ይገነባል | ከባድ ጥገና ወይም ሙሉ ግንባታ(ከመንግስት ድጋፍ ይፈልጋል) |
| Y/ፈ | ሊገነባ የታቀደ ቦኖ ወይም ግንባታ ላይ ያለ ቦኖ | የግንባታ ሥረዉን መጨረስ እንዲሁም የርክብክብ ሥራ | ምንም አይነት የጥገና ሥራ የማያስፈልጋቸው ሆነው ደሽቦርድ ላይ የሚመዘገቡ |
| E/ሠ | ውሃ የሌለበት ጥልቅ ጉድጓድ፣የመከነ ወይም የወደመ ቦኖ፣ የመከነ ምንጭ፣ ውሃ የሌለበት ተቋም፣ የውሃ አገልግሎት መዋጮ መሰብሰብ የማይቻልበት | ቦኖ የሌለው፣ ውሃ ካልተዳረሰበት አካባቢ ጋር አቻ የሆነ | የዚህ ዓይነት ቦኖ በውሃ ቦኖ ዝርዝር ውስጥ አይካተትም(አዲስ ቦኖ የሚያስፈልግበት) |

**<u>ማስጠንቀቂያ፡</u>** ደረጃ በቀጥታ ምን እይነት ሥራ መሠራት እንዳለበት ለማወቅ አይጠቅምም። የማስተካከያ ሥራ መከታተያ ፎርማት ምን አይነት ሥራ መሠራት እንዳለበት የሚያብራራ ማጣቀሻ ሰነድ ነው።

ቀበሌ : ____________________ የማህበር ስም:______________________

| የፍተሻ መዝገብ ላይ ያሉ ችግሮች | መደበኛ እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋል | የሚያስፈልገው የማስተካከያ ሥራ | የጥቅምት ፍተሻ: የ B ችግር — ውማ | የጥቅምት ፍተሻ: የ B ችግር — ውሃ ተጠሪ/ፌዴሬሽን | የጥቅምት ፍተሻ: የ C ችግር — ግንበኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| የተቋም አይነት እና ስም : <u>የጨጨራ ቦኖ</u> | | | በወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ የተጎበኘ ☐ | | |
| ወለሉ ንጹህ አይደለም | ☒ | የየቀኑን ጽዳት ስራ ማደራጀት | ☒ | ☐ | ☐ |
| ቦኖው ላይ ስንጣቆ አለ | ☐ | የውሃውን የላይኛውን ክፍል መስበርና በፎረምወርክ ማጠናከር | ☐ | ☐ | ☒ |

ምሳሌ፦

ቢያንስ አንድ የማስተካከያ ሥራ ኖሮት በውተ እና በፌዴሬሽን ሊሠራ የማየችል ነው። ስለዚህ ፌዴሬሽኑ ልምድ ባለው ኮንትራክተር ሥራውን ሊያሰራ ግድ ነው።ነገር ግን በየዕለቱ የጽዳት ሥራውን በራሱ ሊሠራ ይገባል።(በደበኛ የቦኖ እንክብካቤ ሥራ ሊሠራ ይገባል።)

ለእያንዳንዱ ተቋም ደረጃው በማስተካከያ ሥራው መከታተያ ፎርማቱ ላይ ሊሞላ ይገባል።

**የተቋሙ አንዱ ወቅር ብቻ ደረጃ፣** የደረጃ አሰጣጡ ከዚህ በታች በተቀመጠው ደንብ መሠረት የተቋሙ አንዱ ውቅር ብቻ ደረጃ ከውቅሩ በላይ ያለውን ቧንቧ ጭምር ያካተተ ደረጃ ነው።(ከቦኖ ራስጌ በኩል ያለው የኔት ዎርኩ እዱ ውቅር እና በካከላቸው ያለ ቧንቧ ጭምር ያካትታል)



- **የ"A" ደረጃ ቦኖ**

የሚሠራ ተቋም ሆኖ ምንም አይነት የማስተካከያ ሥራ የሌለው ወይም ሁሉም የማስተካከያ ሥራ የተሠራለት ተቋም ነው።

- **የ"B" ደረጃ ቦኖ፣** የሚሠራ ተቋም ሆኖ ቢያንስ አንድ **የ"B"** የማስተካከያ ሥራ ያለው እና የማስተካከያ ሥራው ያልተሠራለት ተቋም ነው።
- **የ"C" ደረጃ ቦኖ፣** የሚሠራ ተቋም ሆኖ ቢያንስ አንድ **የ" C"** የማስተካከያ ሥራ ያለው እና የማስተካከያ ሥራው ያልተሠራለት ተቋም ነው።
- **የ" D " ደረጃ ቦኖ፣** የማይሠራ ተቋም ነው

<u>**አንድ ቦኖ ውሃው በሚመጣበት አቅጣጫ(ራስጌ በኩል) በላይ በኩል ያሉት ችግሮች በሙሉ የቦኖው የራሱ ችግር ተደርገው ይወሰዳሉ። ደረጃውም ከዚሁ ከራስጌ በኩል ካሉት የኔትዎርኩ ክፍል የከፋው ችግር ያለበት ደረጃ ይሰጠዋል።**</u>

ይህ ሪፖርት የተደረገው የቦኖ ደረጃ የቦነውን የራሱንና ከቦኖው በላይ በኩል ያለውን የኔትዎርክ አጠቃላይ ሁኔታ ያመላክታል።

| ❶ | ❷ |
|---|---|
|  |  |
| የቦኖ 1 ደረጃ የሚወሰነው በቦኖ 1 ሁኔታ ፣ በምንጩ እና ከምንጩ እስከ ቦኖ 1 ባለው የውሀ መስመር ነው። | የቦኖ 4 ደረጃ የሚወሰነው በቦኖ 4 ሁኔታ ፣ በማከፋፈያ 1 ፣ በማከፋፈያ 2 ፣ በማጠራቀሚያ 2፣ በምንጩ እና ከምንጩ እስከ ቦኖ 4 ባለው የውሀ መስመር ነው። |

| | የ ❶ ደረጃ |
|---|---|
| ምንጩ | B |
| ማከፋፈያ 1 | |
| | |
| | |
| የቦኖ1 ብቻ ደረጃ | A |
| የላይኛው ዝቅተኛው ደረጃ | B |
| አጠቃላይ የቦኖ 1 ደረጃ | B |

| | የ ❷ ደረጃ |
|---|---|
| ምንጩ | B |
| ማከፋፈያ 1 | A |
| ማከፋፈያ 2 | A |
| ማጠራቀሚያ 2 | C |
| የቦኖ4 ብቻ ደረጃ | A |
| የላይኛው ዝቅተኛው ደረጃ | C |
| አጠቃላይ የቦኖ 4 ደረጃ | C |


ይህ **በማስተካከያ ሥራ መከታተያው** ቅጽ ላይ መሞላት ይኖርበታል

| | |
|---|---|
| የዚህ ተቋም ብቻ ደረጃ(A,B,C,D,E) | A |
| የላይኛው ዝቅተኛው ደረጃ(A,B,C,D,E) | B |
| አጠቃላይ **የተቋሙ ደረጃ(A,B,C,D,E)** | B |

| | |
|---|---|
| የዚህ ተቋም ብቻ ደረጃ(A,B,C,D,E) | A |
| የላይኛው ዝቅተኛው ደረጃ(A,B,C,D,E) | C |
| አጠቃላይ የተቋሙ ደረጃ(A,B,C,D,E) | C |

## 5. ማለማመድ/ማብቃት

ፍተሻ፣የማስተካከያ ሥራ ልየታ እና ፊር ማስያዝን በተሳካ መልኩ ለመተግበር የሚከተለውን የሥልጠና/ድጋፍ ሥርዓት ፣መከተል ይኖርብናል።




**ደረጃ 1፡ ክልል ግብረ-ኃይል እና የአርአያ ማስተባበሪያ**

ተሳታፊዎች፡

- የዞኑ ግብረ-ኃይል አስተባባሪ
- የዞኑ ባለሞያ
- የዞኑ አርአያ ባለሞያ

የአንድ ቦኖ ፍተሻ እና የማስተካከያ ሥራ ልየታውን(ከምንጭ እስከ ቦኖ) በአንድ ፌዴሬሽን ለየዞኑ ገለጻ ማድረግ

**ደረጃ 2፡ የዞኑ ባለሞያ እና የዞኑ አርአያ ባለሞያ**

ተሳታፊዎች፡

- የወረዳ ማኔጅመንት ቡድን
- ሁሉም የወረዳ ባለሞያዎች
- የወረዳው አርአያ ባለሞያ

የአንድ ቦኖ ፍተሻ እና የማስተካከያ ሥራ ልየታውን (ከምንጭ እስከ ቦኖ) በአንድ ፌዴሬሽን ለየወረዳው ገለጻ ማድረግ

**ደረጃ 3፡ የወረዳ አርአያ ድጋፍ → ለወረዳ ባለሞያ**

ተሳታፊዎች፡

- የወረዳ ባለሞያዎች
- የወረዳው አርአያ ባለሞያ

በየትኛውም ወረዳ ባለሞያ የሚደረገው የመጀመሪያው ፍተሻ እና የማስተካከያ ሥራ ልየታ(ከምንጭ እስከ ቦኖ) መደረግ ያለበት በወረዳ አርአያ ባለሞያ ድጋፍ መሆን አለበት

**ደረጃ 4፡ የወረዳ ባለሞያ ድጋፍ**

- የወረዳው ባለሞያ ስለአሰራሩ ለፌዴሬሽን ኮሚቴዎች ማስረዳት ይኖርበታል
- የውሃ ተጠሪው አጠቃላዩን ሂደት መስክ ላይ ሲሰራ ከወረዳ ባለሞያ ጋር በመሆን ሁለት ሙሉ ኔትዎርክ በየፌዴሬሽኑ(በዞኑ ባለሞያ በዕጣ የተለዩ) ሊሆን ይገባል።

- የውሃ ተጠሪው ቀሪ ሁሉንም በፌዴሬሽን ውስጥ ያሉ ኔትዎርኮችን ፍተሻ( ቼክሊስቱን በመጠቀም) ማካሄድ ይኖርበታል እንዲሁም የተገኙ ችግሮችን እና የማስተካከያ ሥራዎችን ማስታወሻ ሊይዝ ይገባዋል
- የወረዳው ባለሞያው የውሃ ተጠሪው በመስክ የሠራውን የፍተሻ ሥራ በፌዴሬሽን ቢሮ ውስጥ ከውሃ ተጠሪው ጋር በመሆን ስለእያንዳንዱ ኔትዎርክ ችግርና የማስተካከያ ሥራ ሥልታዊ ክለሳ እና ፊር የማስያዝ ሥራ ማድረግ ይጠበቅበታል። **<u>Format n° WS3-F12 "የማስተካከያ ሥራ መከታተያ ፎረማት በመጠቀም" ሊሆን ይገባል።</u>**

## 6.መረጃ ማደራጀት

በዚህ ደረጃ የሚከተሉ መረጃዎች ሊደራጁ ይገባል

- በመስክ የሚሞላ የፍተሸ የፍተሻ ቼክሊስት፡ ***<u>Format n°WS3-F11-V1.0 Diagnosis checklist format</u>*** - በወረዳ ባለሞያ የሚሞላ የማስተካከያ ሥራ መከታተያ ፎርማት፡ **<u>Format n° WS3-F12 Corrective Measure Follow-up</u>** - በሠንጠረዡ መጀመሪያው የቁም ረድፍ የሚሞላ Format n° WS3-F15: Maintenance Plan። የተቋሙን ስም እና ዓይነት እንዲሁም የሚተገበር የማስተካከያ ጥገና መሙላት።

የወረዳ ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያው የፍተሸ መከታተያውን **<u>Format n° WS3-F21 Monitoring – Diagnosis</u>** ማጠናቀርና ለወረዳ ማኔጅመንት ቡድን እና ለዞኑ ፎካል ክትትል ለማድረግ እንዲመች መላክ ያስፈልጋል

## 7. የማስተካከያ ሥራዎች ውሳኔ ማሳወቅና ስምምነት

### 7.1 ከፌዴሬሽን ጋር በጋራ መሥራት

የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ የወረዳ ማኔጅመንት ኮሚቴ በተገኘበት <u>Doc n° WS3-M11a "የፍተሻ እና የማስተካከያ ሥራ በተመለከተ ማብራሪያ ለፌዴሬሽን ይሰጣል።</u>

### 7.2 ለሕጋዊነት ማልበስ

ሁሉም ኔትዎርክ አንዴ ከተፈተሸ እና በማስተካከያ ሥራ ፎርማቱ ላይ ተመዝግቦ ሕጋዊ ከሆነ በኋላ የማረጋገጥ እና የማሳወቅ ሥራው ለውማሬ እና ለወማኮ ከተደረገ በኋላ በመፈራረም ወደ ሥራ ይገባል።

<u>ተሳታፊዎችና ኃለፊነቱን የሚወስድ አካል</u>

- የውሃ ተጠሪ፡ የማስተካከያ ሥራውን ገለጻ ያደርጋል
- የወ/ው/ጽ/ቤት፡ የውሃ ተጠሪውን ይደግፋል
- ቢያንስ ከየውማ 1 ሰው ሥራዎችን ለመተግበር ይመደባል
- የውማሬ አባላት፡ በማስተካከያ ሥራው ተሳትፎ ያደርጋሉ
- ወረዳ ማኔጅመንት ኮሚቴ(ወማኮ)፡ ከኮሚቴው አንድ አባል የማስተካከያው ሥራ መሠራቱን ያረጋግጣሉ

<u>የስብሰባው ዋና አጀንዳዎች</u>

- የእያንዳንዱን ኔትወርክ የማስተካከያ ሥራ ውሃ ተጠሪው በወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ድጋፍ ገለጻ ያደርጋል - ፌዴሬሽንና የውማ ተወካይ የማስተካከያ ሥራውን ተገቢነት በማረጋገጥ በሂደቱ ተሳትፎ በማድረግ ችግሩን ይፈታሉ፤ የፌዴሬሽኑ ሰብሳቢ ማስተካከያ ሥራውን ለመፍታት በፊርማ ያረጋግጣል( ***<u>Format n° WS3-F12 Corrective Measure Follow-up.)</u>*** - የወማኮ ተወካይ ሁሉንም ዓይነት የማስተካከያ ሥራ ያረጋግጣል፤ ምንም ዓይነት የማስተካከያ ሥራ በሠንጠረዡ የC ቁም መስመር ያለመከተቱን በማረጋገጠ መፈረም

ሁሉም ባለድርሻ አካላት የማስተካከያን ሥራውን ለመሥራት መስማማታቸውን በፊርማ ሲያረጋግጡ

- የኔትወርኩን ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚችሉ ጉዳዮች ታሳቢ መደረግ ይኖርባቸዋል
- የውማ፣ውማሬ እና የወ/ው/ጽ/ቤት ሁሉም የB ማስተካከያ ሥራዎችን በራሳቸው አቅም ሊሠሩ ይገባል።(ይህ ካልሆነ ግን ፌዴሬሽኑ በጥገናው ሊወድቅ ይችላል)
- የውማ፣ውማሬ እና የወ/ው/ጽ/ቤት ቢያንስ አንድ የC ማስተካከያ ሥራ መርጠው በራሳቸው አቅም ሊሠሩ ይገባል።(ይህንን ካደረጉ ፌዴሬሽኑ በዳሽቦርዱ አንድ ነጥብ ያገኛል)

### 7.3 ማለማመድ/ማብቃት

የማለማመድ ሥራው በቢሮ ደረጃ ብቻ ካበቃ ሙሉ ክህሎትና እውቀት ሊያስጨብጭ አይችልም

**ደረጃ 1፡ የክልሉ ግብረ-ኃል እና የአርአያ ማስተባበሪያ**

ተሳታፊዎች፡

- የዞኑ ግብረ-ኃይል
- የዞኑ ባለሞያ
- የዞኑ አርአያ ባለሞያ

የልምምድ ጊዜ ማመቻቸት፡ በቢሮ ደረጃ የቲዮሪ እና በመስክ ደረጃ የልምምድ ጊዜ ማመቻቸት

**ደረጃ 2፡ የዞን እና የአርአያ ዞን ባለሞያ**

ተሳታፊዎች

- ወማኮ
- ሁሉም የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ
- የወረዳ አርአያ ባለሞያ

ስለሥራው ትውውወቅ በወረዳ ቢሮ ደረጃ ማድረግ እና የመጀመሪያውን የመስክ ልምምድ በዞኑ ባለሞያ ድጋፍ ማድረግ

**ደረጃ 3፡ የወረዳ አርአያ ደጋፊ → ወ/ው/ጽ/ቤት**

የመጀመሪያው ወ/ው/ጽ/ቤት የመስክ ልምምድ በወረዳው አርአያ ባለሞያ ድጋፍ ይደረጋል

**ደረጃ 4፡ ቀሪ ልምምዶች**

የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ እና የወማኮ በሁሉም ፌዴሬሽን በመገኘት ልምምዱን በቀሪ ፌዴሬሽኖች በማካሄድ ይጨርሱታል።

### 7.4. መረጃ ማደራጀት

በ **Format n° WS3-F15: Maintenance Plan** በተሰኘው ሠንጠረዡ የመጀመሪያ ቁም መስመር ሁሉንም በፌዴሬሽን የሚከናወኑ ተግባራትን ማግኘት ይቻላል። የተቋሙን ስምና ዓይነት እንዲሁም የማስተካከያ ሥራዎችን መጠን በዚሁ መሙላት ያስፈልገል።

የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ፊርማ ተደረገበትን ሰነድ ፎቶ በማንሳት **Format n° WS3-F12 Corrective Measure Follow-up** በተሰኘው ፎርማት በማደራጀት ለዞኑም ባለሞያ ጭምር መላክ ያስፈልጋል